# የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና ሁመራ ችግር መፍትሔው ምንድነው?

ይህ የተለያዩ ቦታዎችን የሚያካትተው በአብዛኛው ግን በወልቃይት ስም የሚጠራው ቦታ የሚገኘው፣ በሰሜን ምዕራብ የኢትዮጵያ አካባቢ ሲሆን፣ በምዕራብ በኩል ከሱዳን ጋር፣ በሰሜን በኩል ደግሞ ከኤርትራ ጋር፣ በሰሜን ምስራቅ በኩል ከትግራይ ጋር ይዋሰናል፡፡ ይህ አካባቢ ከትግራይ ጋር በተከዜ ወንዝ አማካኝነት በተፈጥሮ ደንበር የተከለለ ነው[1]፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረው የኢትዮጵያ አስተዳደር በጠቅላይ ግዛት ከዛም ክፍለ ሀገር በነበረበት ጊዜ፣ ከላይ የተጠቀሰው ቦታ፣ ቀድም ብሎ በበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት[2] በኋላም ጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ ነበረ፡፡ ቀደም ብሎም በየአካባቢ ባላባቶች በሚተዳደርበት ጊዜም፣ ይህ አካባቢ የበጌምድር አካል ነበር፡፡[3,4]

የዚህ ቦታ ኗሪ ህዝብ ዋና መነጋገሪያ ቋንቋው አማርኛ ሲሆን፣ ከተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ ዜጎች ጋር ሰለሚዋሰን፣ ትግርኛም፣ አረብኛም ይናገራል፡፡

ቦታው በለምነቱ የታወቀ፣ ለገበያ በቀጥታ የሚቀርቡ ሰብሎች ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች የሚገኙበት ነው፡፡ ምንም እንኳን የበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት አካል ቢሆንም፣ እንደ ማንም ኢትዮጵያዊ ከኤርትራ፣ ከትግራይ፣ ከበጌምድርና ሰሜን የተለያዩ ባለሀብቶች በቦታው ገንዘብ በማውጣት ሰፋፊ እርሻዎችን ያሳርሱ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ የጎረቤት የትግራይ ክፈለ ሀገር ኗሪዎችም ሰብል ለአጨዳ በሚደርስበት ወራት ወደ አካባቢው እየዘለቁ ሠርተው በመመለስ በሥራ ዕድሉ ተጠቃሚ እንደነበሩ ግልፅ ነው፡፡

ሆኖም በኢትዮጵያ የደርግ መንግሥት ሥልጣን በያዘ ማግሥት ሰፋፊ የግል እርሻና ባለሀብትነትን በአዋጅ በመሰረዙ፣ በቦታው የነበሩ ባለሀብቶች ሥራቸውን መቀጠል አልቻሉም፡፡ ተያይዞም የደርግን መንግሥት የሚቃወሙ ሀይሎች፣ በተለይም የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት(ኢድሕ) በዚህ አካባቢ በመጠለል ደርግን መዋጋት ብቻ ሳይሆን እርስ በራሳቸው ሲዋጉ እንደነበረና በዚህ ምክንያት የወልቃይትና አካባቢው ህዝብ ኑሮ የታወከ እንደ ነበር ግልፅ ነው፡፡ ቀጥሎ የመጣው ደግሞ ትግራይን ለብቻ ሀገር አድርጎ መመስረት ዋናው አላማ ያደረገ፣ የትግራይ ህዝብ ነፃነት ግንባር (ትሕነግ) ወይም በትግርኛ ህወሓት የሚባል ከጎረቤት ከትግራይ ክፍለ ሀገር የተነሳ ሀይል ነበር፡፡ ትህነግ ወደ አካባቢው ከገባ በኋላ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ አመቺ የሆነለት፣ በወልቃይት ምድር ተሻግሮ ከጎረቤት አገር ከሱዳን ጋር መገናኘት መቻሉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከደርግ ጋራ ሲያደርገው ለነበረው ትግል ከፍተኛ መሠረትና ጥንካሬ ይሠጠው ነበር፡፡ የወልቃይትና አካባቢው ኗሪም በደርግ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ሰለነበረው፣ እነዚህ ደርግን የሚፋለሙ የተለያዩ ሀይሎችን አስጠልሎ ነበር፡፡

ትህነግ ይህንን ለትግሉ አመቺ የሆነውን ቦታን ከተቆጣጠረ በኋላ፣ ፍላጎቱን በማስፋት፣ ቦታውን ሙሉ በሙሉ የራሱ ለማድረግ በማሰብ ተወላጆችን በመሰብሰብ፣ ከአሁን ጀምሮ የትግራይ አካልና ትግሬዎች ናችሁ ብሎ መናገር በመጀመሩ፣ ኗሪዎችም የጎንደር አካል መሆናቸውን፣ ከዛም አማራዎች መሆናቸውን በመግለፅ በየስብሰባ መድረኮች ተቃውሟቸውን አሰሙ፡፡

ከዚህ በኋላ ግን ትህነግ፣ በፊት ለፊት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን በመገንዘቡ፣ ቦታውን ወደ ራሱ ለማካለል ቆርጦ በመወሰን የተለያዩ ግልፅና ሽፍን የሆኑ ጥቃቶችን በወልቃይት ህዝብ ላይ ማድረስ ጀመረ፡፡ ይህንን ማድረግ የጀመረው በ1984 አመተ ምህረት ነበር፡፡ ትህነግ በተወላጆቹ ላይ ያደርሳቸው የነበሩ የተለያዩ ጥቃቶችን ባጭሩ ለመግለፅ፡

---

[1] ጀምስ ብሩስ (Travels to Discover the Source of the River Nile, 1776, Chapter X, p 248)

[2] የትግራይ ተወላጅ የሆኑት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ልጅ የሆኑት ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም በጻፉት የትውልድ አደራ በተባለው መፅሐፋቸው የትግራይ ጠቅላይ ገዥ በነበሩበት ጊዜ የወልቃይትና አካባቢው የበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ውስጥ እንደነበር በምስክርነት አስፍረዋል፡፡

[3] Welkait, Ethiopia: Geo Strategic importance and the Consequential Annexation by TPLF፣ Wosenyelew Tedla & Moges kelklie: https://www.hornafricainsight.org/post/welkait-ethiopia-geo-strategic-importance-and-the-consequential-annexation-by-tplf

[4] አቻምየለህ ታምሩ፣ መፅሐፍ "የወልቃይት ጉዳይ፤ የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና ሁመራ የወሰንና የመልክዓ-ምድር ታሪክ ምርምር ውጤት (ከ323 ዓ.ም. እስከ 1983 ዓ.ም.)

1ኛ. ከተወላጆች መሀከል የሀገር ታሪክ አዋቂዎችን፣ ደጋጎችን በውድቅት ሌሊት በማፈን መውሰድና በጅምላ መግደል፡፡ ከነዚህ መጀመሪያ ታፍነው የተወሰዱ 31 ሰዎችን ሁኔታ የታፈኑት ሰዎች ልጆች በምስክርነት የሚገልፁት ነገር ነው[5]፡፡

2ኛ. ከደጋጎች በተጨማሪ ወንዶችን፣ ወጣቶችንም እያፈኑ ሰለወሰዱ፣ የቀሩት ሴቶች ራሳቸውን በግብርና ማስተዳደር ሰላልቻሉ የእርሻ ቦታቸውን እየለቀቁ በመሄድ ወደ ጎረቤት አገር ወደ ሱዳን አንዲሰደዱ ተገደዋል፡፡ በዚህም፣ ሰዎቹ የለቀቋቸውን ቦታዎች ከትግራይ ክፍለ ሀገር በመጡ የትግራይ ተወላጆች እንዲያዙ አደረጉ፡፡

3ኛ. የሚች ሚስቶችን በማስገደድ በማግባት ልጅ ማስወለዱን እንደ ዕቅድ በመያዝ፣ አንድ የትግራይ ተወላጅ ከተለያዩ የወልቃይት ሴቶች ልጆች ያስወልድ ነበር፡፡ በተጨማሪም፣ አስገድደው ያገቧቸውን ሴቶች ከሁለትና ከሶሰት አመት በኋላ በመፍታት የሴቶቹን ንብረት ይካፈሉ ነበር፡፡ ንብረት ከተካፈሉ በኋላም፣ ከትግራይ የራሳቸውን ሴቶች ወይም የመጀመሪያ ሚስቶቻቸውን በማምጣት በተካፈሉት ንብረት ላይ ይኖሩ ነበር፡፡

4ኛ. የመነጋገሪያ ቋንቋውን ሙሉ በሙሉ ወደ ትግርኛ ለመቀየር፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ትምህርት በትግርኛ ቋንቋ ብቻ እንዲሠጥ አደረጉ፡፡

5ኛ. በየአድባራቱ ስብከትና ትምህርት በአማርኛ እንዳይሠጥ መከልከል ብቻ ሳይሆን ካህናቱን በትግርኛ እንዲያስተምሩ ያስገድዱ ነበር፡፡ ይህን የተቃወሙ ስማቸው የሚጠቀስ ካህናት ከሌሎች ወንዶች ጋር እየታፈሱ በየጫካው በጅምላ መገደላቸውን በቪዲዮ የተደገፉ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው አንድ አሳዛኝ ሁኔታ፣ በትግርኛ አልሰብክም ያለ፣ ቄስ ገብረመድሕን የሚባልን ካህንን በሌሊት አድፍጠው መንገድ ላይ ከደበደቡ በኋላ ምላሱን ቆርጠው ትተውት እንደሄዱ እናም ካህኑ በደረሰበት ጉዳት ህይወቱ ማለፉን በወቅቱ የነበሩ ምስክሮች ይገልፃሉ፡፡

6ኛ. በኗሪዎች ላይ በሚደርሰው የማያባራ አፈናና ግድያ ምክንያት በህይወት የተረፉ ሰዎች ወደ ጎረቤት አገር ወደ ሱዳንና ከዛም አልፎ ወደ አሜሪካ፣ አውስትራሊያ ድረስ ተሰደዋል፡፡ የተሰደዱት ሰዎች ለቀው የሄዱትን የከተማም ሆነ የገጠር ቦታ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ  ከትግራይ የመጡ ትግርኛ ተናጋሪዎች እንዲሠፍሩበት አድርገዋል፡፡

7ኛ. በህዝቡ ላይ ይፈፅሙት የነበረው ወንጀል ሕገወጥ መሆኑን ራሳቸውም የተረዱት ሰለነበር፣ አፈናዎችና ግድያዎች የሚካሄዱት በሌሊት ነበር፡፡ ሰዎች የሚታሠሩባቸው ቦታዎች ደግሞ ከሰዎች ራቅ ባሉ ጫካዎች ውስጥ ነበር፡፡ ከእስር ቤቶቻቸው በክፉነታቸው በስፋት የሚታወቁት በትሕነግ አጠራር ባዶ ስድስት የሚባሉ፣ መሬት ውስጥ የተቆፈሩ ማጎሪያ ቦታዎች ናቸው፡፡ በአነዚህ ባዶ ስድስት በሚባሉ እስር ቤቶቻቸው ያደርጉት ከነበረው ዘግናኝ ድርጊቶች አንደኛው፣ በጉድጓዶች መውጫ ላይ፣ የማይነድ ግን ብዙ ጭስ የሚፈጥር የተለየ አትክልት በሳት በመለኮስ በጉድጓዱ ውስጥ ያሉ ሰዎችን በጭስ አፍነው ይገድሉ ነበር፡፡ ይህ ድርጊታቸውም በወልቃይት ሰዎች ብቻ ሳይሆን እነሱን ይቃወማሉ ባሏቸው በትግራይ ሰዎች ላይ የተፈፀመ ነው[6]፡፡ በለአርባ አመታት ሲፈፅሙት የነበረውን የጅምላ ግድያና የጅምላ መቃብር በቅርቡ በጎንደር ዩኒቨርስቲ አጥኝዎች ለህዝብ በይፋ የቀረበ ጥናት መግለጫ በመረጃነት ያሳያል[7]፡፡

8ኛ. የጅምላ ግድያዎችን ቀደም ብለው ሲያካሂዱ የነበሩ ለመሆናቸው ብዛት ያላቸው የጅምላ መቃብሮች ይመሰክራሉ[8]፡፡ በተጨማሪም፣ ባስነሱት ጦርነት ተሸንፈው የወልቃይትን መሬቶች ከመልቀቃቸው በፊት ማይካድራ በተባለ ቦታ ትግራይ ያልሆኑ በተለይም የአማራ ተወላጆችን በተገኘው መንገድ በብዛት መግደላቸው የቅርብ ጊዜ በመረጃ የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፡[9]

---

[5] ከታፈኑትና ከተገደሉት ሰዎች የአንደኛው ልጅ የሆኑት የወይዘሮ አልማዝ እንደሻው የምስክርነት ቃል

[6] የቀድሞ የትህነግ አባል የነበሩ የአቶ ገብረመድህን አርአያ ማስታወሻ፤ "ዝሆን ላይ የሚጮህ እብድ ውሻ ብቻ ነው"፣ 09/15/2016

[7] የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጥናት ውጤት መግለጫ (Unpublished)

[8] Ann Garrison. April 27, 2022: https://blackagendareport.com/notes-wartorn-ethiopia-part-iii-crimes-tigrayan-peoples-liberation-front

[9] Report of the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC)/Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights (OHCHR) Joint Investigation into Alleged Violations of International Human Rights፡ https://www.un.org/sexualviolenceinconflict/wp-content/uploads/2022/02/report/report-of-the-ethiopian-human-rights-commission-ehrc/OHCHR-EHRC-Tigray-Report.pdf

ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች ሲፈፅሙ፣ አላማው ግልፅ ነበር፡፡ የቦታውን ተወላጆች ቁጥር በአፈናና በግድያ፣ በማሰደድም መቀነስ፣ በምትኩ ትግርኛ ተናጋሪ ሰዎችን ማስፈር፤ የቦታው ታሪክ ለትውልድ እንዳይተላለፍ የአካባቢውን ታላላቅ ሰዎች መግደል፣ ማሰደድ፤ የአማርኛ ቋንቋ እየመነመነ እንዲሄድ፣ አማርኛ በአደባባይ እንዳይነገር፣ ትምህርትም በትግርኛ ብቻ እንዲሠጥ ማድረግ፤ የኗሪውን ገፅታና ቁጥርም በመቀየር የትግራይ አካል ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

የደርግ መንግስት ሥልጣን እስከያዘበት ጊዜ ድረስ ማንም ኢትዮጵያዊ ባለሀብት ያሳርስበት የነበረ ይህ ለም ቦታ፣ ባለው የተፈጥሮ ሀብት ምክንያት በጉልበት ወደ ትግራይ እንዲካተት ማድረግ ከጥዋቱ ሲነሱ ያለሙትን ትግራይን ገንጥሎ ለብቻ ሀገር የማቋቋም የትህነግ ረጅም ርቀት አላማ፣ ወሳኝ ቦታ ነው፡፡ ይህንን ሀገር የመመስረት ሀሳብ አቋርጠው የማያውቁ መሆኑን ለመረዳት፣ ለሀያ ሰባት አመታት በኢትዮጵያ ላይ ሙሉ ሥልጣን በነበራቸው ጊዜ የነፃነት ግንባር(ህወሓት) የሚለውን የፓርቲ ስም ሳይቀይሩ መቆየታቸውን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም፣ ይህንን አካባቢ በማንአለብኝነት በጉልበት[5] ነቅሰው ወደ ትግራይ ቢያጠቃልሉና አዲስ የትግራይ ካርታ ቢያወጡም፣ የትግራይና የበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር በተከዜ ወንዝ በደንበርነት የተለያዩ አንደሆነ እኤአ ከ1991 በፊት የወጡ ካርታዎች በግልፅ የሚያሳዩት ሀቅ ነው፡፡

የትህነግ የመገንጠል አላማና ይህንንም ግብ ለማሳካት የሚያደርገው እንቅስቃሴ መሠረቱ የወልቃይትና አካባቢውን ምድር የኔ ነው በማለት ድርቅ ያለ አቀራረብ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሰለዚህ በተወላጆቹ ላይ ለአርባ አመታት ያላባራ ጥቃት፣ እንግልትና መከራም የደረሰው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

የወልቃይትና የአካባቢው ህዝብ ዋና ጥያቄ ከአርባ አመታት በላይ ለደረሰበት ግፍና በደል ፍትህ ማግኘት ነው፡፡ ኗሪዎቹ የሚያቀርቡት የፍትህ ጥያቄ፣ ማንነታቸው ተከብሮ ለዘመናት ወደነበሩበት አስተዳደር ተመልሰው በሰላም መኖር፣ ልጆቻቸውን ማሳደግና ማስተማር እንዲችሉ ነው፡፡ ኗሪዎቹ፣ ቀድም ብሎ እንደነበረው ሁሉ ከጎረቤት ክፍለ ሀገር የትግራይ ተወላጆች ጋር በሰላም አብሮ የመኖር ችግር አልነበረባቸውም የለባቸውም፡፡

የዚህ የፍትህ ጥያቄ ባግባቡ መልስ አለመሠጠት፣ ሲበደል የኖረውን ህዝብ እንደገና መበደል ብቻ ሳይሆን፣ ለትህነግ የዕብሪተኛነት የመገንጠል አላማ ዋና መሠረት የሆነውን በጉልበት ነጥቆ ወስዶት የነበረውን ይሕንን ቦታ መልሶ መሥጠት ነው፡፡  በተጨማሪም፣ ለፍትህ ጥያቄው ትክክለኛ መልስ አለመስጥት፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው፣ በበደል ላይ በደል በመጨመር ለአርባ አመታት ሲበደል የነበረን ህዝብ አማራጭ በማሣጣት ራሱ በተቻለው አቅሙ መብቱን እንዲያስጠብቅ ስለሚያስገድደው ለአካባቢው ብቻ ሳይሆን፣ ለጠቅላላው ኢትዮጵያ ታላቅ ችግር የሚፈጥር ሁኔታ ነው፡፡ ሰለዚህ ይህ የፍትሕ ጥያቄ አጠቃላይ የሀገሪቱ ዜጎች ጥያቄም ሰለሆነ የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ትክክለኛውን ፍትሀዊ መልስ እንዲሠጥ የሚያስገድድ ጥያቄ ነው፡፡

የወልቃይትና አካባቢው፣ ባለው የመልክዐ ምድር አቀማመጥ ምክንያት ከሱዳንና ከኤርትራ ጋርም የሚዋሰን በመሆኑ፣ ይህ አካባቢ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በባሕሪው ፀረ-ኢትዮጵያ[6] በሆነው በትዕቢተኛው ትህነግ እጅ ሥር እንዲወድቅ ከተደረገ፣ ሊነሳ የሚችለውን የሉዐላዊነትና የሰላም ችግር መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ይህ የፍትህ ጥያቄ አለመመለስ ኢትዮጵያ ባለችበት ሁኔታ እንደ አንድ ሀገር መቀጠል መቻሏን የሚያናጋ በመሆኑ፣ የሀገሪቱ የህልውና ጥያቄም ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ጥያቄ ባግባቡ እንዳይመለስ የሚያደርግ የውስጥም ሆነ የውጭ ተፅዕኖ የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡ በተለይም ትህነግ ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ በወልቃይት ሲያካሂድ የነበረውን የዘር ማፅዳት ዘመቻ ያላዩና ያልሰሙ በመመስል፣ በወቅቱ በትህነግ አነሳሽነት ከተፈጠረው ግጭት በኋላ፣ የምዕራባውያን የዜና አውታሮችና የምዕራባውያን መንግሥታት፣ የትህነግን ዕኩይ አላማ በመቀበል “ምዕራብ ትግራይ” በሚል ስም የትግራይ ተወላጆች ላይ “የዘር ማፅዳት” ዘመቻ እየተካሄደ ነው በማለት የሚያስተጋቡት ፕሮፓጋንዳ ከዕውነታ የራቀ ኢትዮጵያን ወደ የማያባራ ቸግር የሚገፋና ሉዐላዊነቷን የሚደፍርና የሚያስደፍር ድርጊት ነው፡፡

ይልቁንስ የዚህ ጥያቄ በአግባቡ መመለስ፣ በአጉል ምኞት የትግራይ ሪፓብሊክ እፈጥራለሁ በማለት የትግራይ ተወላጆችን ለማያባራ ጦርነትና መከራ የሚዳርገውን የትህነግን ትዕቢትና ህልም የሚቀጭ ሰለሆነ ውሎ አድሮ ወደ ዘላቂ ሰላም የሚያሸጋግር ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ይህ ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ የወቅቱ አንገብጋቢ የህልውና ጥያቄ መሆኑን በጥብቅ የተገነዘብን እንደ ማንም ተቆርቋሪ ዜጋ፣ ይህ የፍትህ ጥያቄ ባግባቡና ባስቸኳይ እንዲመለስ ጥሪ እያቀረብን፣ ሌሎች ወገኖችም በተመሳሳይ ሁኔታ ይህንን ጥሪ እንዲያስተጋቡ በትህትና እንጠይቃለን፡፡